// ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
efdpu@aol.com www. Finote.org
**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

# ዜና ዘገባ

**ነሐሴ 1 ቀን 2002 ዓ.ም**

***በየወያኔ ቡድን መሪዎች ለምንጠራው አንድ ወደፊት እያሉ ነው***

***ባለስልጣናት ከሀገር እንዳይወጡ ታገዱ፤***

***ጅቡቲ የኢትዮጵያን ንብረት እያበላሸች መሆኑ ታወቀ፤***

***የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት እርስ በርስ ሽኩቻ ውስጥ ገቡ፤***

ለ19 ዓመታት በስልጣን ላይ የነበሩት ባለስልጣናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጭንቀት ተውጠውና በፍርሃት እየራዱ መጪው መስከረምን ወር እየተጠባበቁ መሆኑን ለወያኔ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አጋለጡ፡፡

በስልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት የሀገርና የህዝብ ሀብት ሲመዘብሩና ሲቦጠቡጡ የኖሩት እነዚሁ ባለስልጣናት በመጪው መስከረም ወር መጨረሻ ላይ ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው የካቢኔ ለውጥ እና ሹም ሽር ምክንያት ከስልጣናቸው ሊነሱ (ሊባረሩ) እንደሚችሉ እየተነገረ ባለበት በአሁኑ ወቅት ሁሉም በድንጋጤ ከንፈራቸው ደርቆ...... ምላሳቸው ተጣብቆ . ፊታቸው ጠውልጐ የሚይዙትና የሚጨብጡት ጠፍቷቸው እንደሚገኝ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጥቆማ አስታወቀ፡፡

ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሠ እስከ ተራ የቀበሌ ሹም ........ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ስዩም መስፍን እስከ ወረዳ ሹማምንቶች ድረስ ሹም ሽር ይደረጋል ተብሎ ዝግጅት እየተደረገ በመሆኑ ባለስልጣናቱ በድንጋጤ ላይ መሆናቸውን ያጋለጠው የደረሰን ጥቆማ እስከ ዛሬ ድረስ በሀገሪቱ ህዝብ ላይ በማህበራዊም፣ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ላይ ጫና ፈጥረው እንደልባቸው ሲምነሸነሹ እንዳልነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በድንጋጤና በፍርሀት አመመኝ እያሉ ወደ ጤና ተቋም መመላለስ መጀመራቸውን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጥቆማ አጋልጧል፡፡

ሕዝቡ ጫንቃ ላይ ተጐልተው ሲያናጥሩና ሲሳለቁ የኖሩት . . . ባለስልጣናት ከሀገሪቱ ገንዘብ ላይ ዘርፈው ሀብት ያከማቹ ቢሆንም በቅርቡ ከሚደረገው ሹም ሽረት ጋር ንብረት እንዲያስቆጥሩ ይደረጋል ተብሎ በመወራቱ ባለስልጣናቱ በራሳቸው ስም ያሉትን ጥሬ ሀብት እና ኩባንያዎች ጭምር በዘመዶቻቸው እና በቅርብ ሰዎቻቸው ስም እያዞሩ መሆኑን ጥቆማው አስረድቷል፡፡

በተለይ ከፍተኛ የሀገርና የህዝብ ሀብት ዘርፈው አከማችተዋል የተባሉ ባለስልጣናት ባደረባቸው ስጋት እና ጭንቀት የተነሳ በቀን ሁለት ሶስት ጊዜ ሆስፒታል ለመመላለስ የተገደዱ ከመሆኑም በላይ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሳይቀር እየቀዘቀዘ መምጣቱንም ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጥቆማ አብራርቷል፡፡

በተለያዩ የህክምና ተቋሞች እየተመላለሱ ከመታከማቸውም በተጨማሪ ወደ ውጭ ሀገር ሔደው እንዲታከሙ ሪፈራንስ እንዲፃፍላቸው ሐኪሞቻቸውን ቢጠይቁም ከአቅም በላይ ስላልሆነ አይፃፍም እየተባሉ እየተከለከሉ ሲሆን ገሚሶቹ ሪፈራንስ ቢፃፍላቸውም ከሀገር እንዳይወጡም መመሪያ መተላለፉን ጥቆማው አስረድቷል፡፡

መለስ ከህዝብ ድጋፍ አገኛለሁ በሚል በራሱ ካድሬዎች እና ባለስልጣናት ላይ እርምጃ ይወስዳል እየተባለ በመነገሩ ጭንቀት ውስጥ ከመውደቃቸውም በላይ ከህዝብ የዘረፉትን ሀብት እና ንብረቶቻቸውን እያሸሹ አንዳንዶቹ አስቀድመው ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ወደ ውጭ ሀገር እየላኩ መሆኑን የደረሰን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጥቆማ አንዳንዶቹ በድንጋጤ በተነሳ ህመም ለከፋ ደረጃ መዳረጋቸውን አብራርቶዋል፡፡

ከዚህ በተጉዋዳኝ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ግልገል ሹማምንቶች ላይ ጠንከር ያለ ግምገማ እየተደረገ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የምንጠራ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚችል ምንጮቹ ከወዲሁ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡

ከሐምሌ ወር አጋማሽ ጀምሮ በግልገል ባለስልጣናት ላይ የሹም ሽረት እርምጃው የተጀመረ ሲሆን፣ እስከ ዛሬ ድረስ ሲሞካሹና ሲወደሱ የነበሩት በሙሉ እየተባረሩ ቤት ንብረታቸው እየቆጠረ እንደሚገኝም ጥቆማው ገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ከተሞች የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ አስተዳደር ተብለው ተሰይመው የራሳቸው ካቢኔና ከንቲባ የነበራቸው ሲሆን በቅርቡ በተጀመረው ምንጠራም የመጀመሪያ ሰለባ ለመሆን እንደቻሉ ጥቆማው ገልፆ በተለይ የዱከም ፣ የመናገሻ፣ የቡራዩ እና የሰበታ ካቢኔ እየታመሱ እንደሚገኝ ጥቆማው አብራርቷል፡፡

በዚህም መሠረት የሰበታ ካቢኔ በሹም ሽር ሒደቱ እየተናጠ ከሆመኑም በላይ የተሰናበቱ ባለስልጣናት ያላቸው ንብረት እንዲመዘገብ ኮሚቴ ተዋቅሮ ስራውን እያከናወነ ሲሆን አንዳንድ ባለስልጣናት ሀብትና ንብረታቸውን በዘመዶቻቸው ስም አዛውረው ከሀገር እየጠፉ እንደሚገኝም ታውቋል፡፡

የዱከም እና የመናገሻ ካቢኔም ሙሉ ለሙሉ የተነሳ ከመሆኑም ባሻገር የመናገሻ ከንቲባ የነበረው ግለሰብ ለእስር ተዳርጐ ሌሎች የካቢኔ አባሎች እየታሰሱ ቢፈለጉም ያልተገኙ መሆኑን ያጋለጠው የደረሰን ጥቆማ እያንዳንዱ ካቢኔ በ10 ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እንዳላቸው ጨምረው ገልፀዋል።

ከ10ኛ ክፍል በታች ሆነው የወያኔን ፖለቲካ ያራምዱ የነበሩት ደናቁርት ባለስልጣናት እንደልባቸው በህዝብ ላይ ሲጫወቱና የሀገርን ሀብት ሲቦጠቡጡ ሀይ የሚላቸው ጠፍቶ ዛሬ የውስጥ ፖለቲካቸው ሲበላሽ ለመጠገን ሲሉ ብቻ ይህን እርምጃ መውሰዳቸው ተገቢ ቢሆንም ጊዜው ያለፈበት እና የዘገየ እርምጃ መሆኑን መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በቁጭት እየገለፁ ይገኛሉ።

በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ ከተማ ካቢኔዎች ላይ የተጀመረው ምንጠራ በአዲስ አበባ መስተዳድርም በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ እንደሚጀመር የጠቆሙት ምንጮች ለዚህም ይረዳ ዘንድ ግምገማ መጀመራቸው ታውቋል።በዚሁ በሚደረገው ግምገማ ላይ ግለሰቡ ያለው እውቀት ሳይሆን ለወያኔ ቡድን አጎብድዶ የሚገዛ መሆኑና ድርጅቱ የሰጠውን ግዴታ መወጣት አለመወጣቱን ዋነኛ መስፈርት እየተደረገ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

ስልጣን የሚሰጣቸው ሹማምንቶች አስቀድሞ ተመርጠው በየማሰልጠኛ ካምኘ ውስጥ ታጉረው የወያኔን ፖለቲካ እየተጠመቁ ሲሆን በቅርቡም በይፋ ተመርቀው ስራ ምድብ እንደሚሰጣቸውና ተሰናባቾቹም እንዳያኮርፉ የማስተዛዘኛ ምደባ እንደሚደረግላቸው ታውቋል።

የወያኔ ቡድን ከውስጥ ያለበትን የሽኩቻ ፖለቲካ መፍትሔ ለመስጠት ሽብ ረብ እያለ ባለበት በአሁኑ ወቅት ጅቡቲ በምትወስደው ተደጋጋሚ እርምጃ የተነሳ ከፍተኛ የራስ ምታት እንደሆነበት ታወቀ።

በአመት ሁለት እና ሶስት ጊዜ በላይ የወደብ ታሪፍ እየጨመረች በኢትዮጵያ ነጋዴዎች እና ባለሀብቶች ላይ እየቀለደች ያለችው ጅቡቲ ሰሞኑን ሌላ አዲስ የመበዝበዣ ስልት ይዛ ብቅ ማለቷ ታውቋል።

ከውጭ ሀገር መጥተው ጅቡቲ ወደብ የደረሱት መርከቦች የጫኑት እቃ እንዳይራገፍ በመከልከሏ ለቀናት ያህል እቃዎች እንዲቆዩ እየተደረገ ከመበላሸቱም በተጨማሪ ታሪፉ ከእቃው በላይ እንዲያሻቅብ እያስገደደች መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ በስዩም መስፍን የሚመራው አንድ ቡድን ወደ ጅቡቲ ተልኮ የነበረ ቢሆንም ሳይሳካለት መመለሱን ምንጮቹ ገልፀው ሰሞኑንም በዑጋንዳ በተደረገ የመሪዎች ስብሰባ ላይ የነበረው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ወደ ሀገር ቤት ሲመለስ እግረ መንገዱን ጅቡቲ ጎራ ብሎ የነበረ ቢሆንም እሱም እንደ ስዩም ሳይሳካለት እንደቀረና በውርደት እንደተመለሰ ገልፀዋል።

ለጅቡቲ ኘሬዘዳንት እስማኤል ጌሌህ እና ባለቤቱ ጭምር በሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ቦታ በነፃ ተሰጥቷቸው ዛሬ ወደ ውጭ ሀገር የሚሸጥ ስንዴ እያመረቱ እና እያወጡ እየሸጡ ባለበት....... በደብረ ዘይት ሆራ ሀይቅ ዳርቻ ለሆቴል እና መዝናኛ ........በድሬዳዋ ለሆቴል መስሪያ ቦታ...... በአዲስ አበባ መኖሪያ ቪላ በነፃ ተሰጥቷቸው ባለበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ንብረቶች በህጋዊ መንገድ ወደ

ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ሰበብ እየፈጠሩ ለከፍተኛ ኪሳራ እየዳረጉ ከመሆኑም ባሻገር የኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ንብረት በስብሶ እንዲቀር ሆን ብለው እየሰሩ መሆኑም ታውቋል።

ጥቃቅንና አነስተኛ ሀገራት ተርታ የምትመደበው ይህችው ጅቡቲ ወያኔ በዘረጋላት እና በፈጠረላት ዕድል ተጠቅማ የኢትዮጵያን ህዝብ ሀብት እያግበሰበሰች ያለችው አልበቃ ብሏት የኢትዮጵያውያን ንብረት በወቅቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ በማድረጎ እቃዎች እየተበላሹ ከመሆኑም በላይ የቀረጥ ክፍያው ከተጫነው ዕቃ በላይ በመሆኑ ነጋዴዎች ለከፍተኛ ኪሣራ እና እንግልት እየተዳረጉ እንደሚገኙ ለመረዳት ተችሏል።

ለጅቡቲው ኀሬዘዳንት እጅ እየነሱና እያጐበደዱ የኢትዮጵያን ህዝብና ጥቅም አሳልፈው እየሰጡ ያሉት እነ መለስ በነጋዴዎች ላይ አልፍ ተርፎም በህዝቡ ንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሳይከነክናቸው መልሰው መሞዳሞዳቸው እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ያለው የደረሰን ዘገባ ባለፈው ሳምንት ብቻ ከ400 በላይ የጭነት መኪኖች ያለ ጭነት ባዶዋቸውን ከጅቡቲ እንዲመለሱ መደረጉን አጋልጠዋል።

በሀገርና በህዝብ ላይ እየተጫወቱ የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት የራሳቸው አልበቃ ብሎ ለጉረቤት ሀገር አሳልፈው ሰጥተው ብጥስጣሽ ሀገር የሆነችው ጅቡቲ በዜጐች ላይ እና በሀብታቸው ላይ እየተጫወተች መሆንዋም የሚያበሳጭ ነው ሲሉ ሹፌሮች በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በተያያዘ ዜና በቅርቡ ከጅቡቲ ጋር በገቡት ውዝግብ ምክንያት በሀገሪቱ የነበሩትን ሁለት የደረቅ ወደቦች ወደ አራት ከፍ በማድረግ ተወስኖ ስራ ሊጀመር መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በባለስልጣናት መሀከል መግባባት ጠፍቶ ከፍተኛ ሽኩቻ ውስጥ እንደገቡም አጋልጠዋል።የጅቡቲ ወደብ ስራ ከሁለት ወር በሁዋላ የሚያቋርጥ በመሆኑ ለዚሁ ይረዳ ዘንድ በሱዳን በሱማሊያ እና በኬንያ ወደቦች ለመጠቀም እየተዘጋጁ ባለበት በዚህ ወቅት በመተማ ሊሰራ የጣቀደውን የደረቅ ወደብ አንድ የህወሀትከፍተኛ ባለስልጣን በመቃወሙ ስራው እስከ ዛሬ ሳይጀመር እንደቆየም ጨምረው አስረድተዋል።

የህወሀቱ ባለስልጣን ደረቅ ወደቡ በትግራይ ክልል ውስጥ መሰራት አለበት ብሎ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም የብአዴኖች በበኩላቸው ለሁሉም ቅርበት ያለው ሱዳን ጠረፍ የሚገኘው የአማራ ክክላዊ መስተዳድር በመሆኑ እዚሁ እኛ ክልል ሊሰራ ይገባዋል በሚል ውዝግብ ውስጥ እንደገቡ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ለሀገር እና ለህዝብ ማሰብ የማይችሉ የአዕምሮ ደሀዎች የሆኑት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት ዛሬም እራሳቸው በዘረጉት ከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲያቸው እርስ በርስ እየተነታረኩ መገኘታቸው እጅግ አሳፋሪ እና አሳዛኝ ነው ።